# የምርጫ ቀን ምዝገባ

VOTE 2025

*በምርጫው ቀን፡ በተመደበሎ የምርጫ ቦታ ለመመዝገብ፡ ከታች ከተዘረዘሩት የመኖርያ ቤት ኣድራሻ ማረጋገጫዎች ውስጥ ኣንዱን ማምጣት ኣለብዎ*

## 1 ወቅታዊ ስምዎና ኣድራሻዎ ያለበት የመታወቅያ ወረቀት

- ህጋዊ የሆነ የሚኖሶታ የመንጃ ፈቃድ፡ የለማጅ ፈቃድ ወይም የመታወቅያ ወረቀት፡ ወይም ለእነዚህ የተቀበሉት ደረሰኝ ካለ
- ስም፡ ኣድራሻ፡ ፎቶ/ስዕል፡ ፊርማ ያለበት የጎሳ የመታወቅያ ወረቀት

## 2 ፎቶዎ/ስዕሎ በተጨማሪም ወቅታዊ ስምዎና ኣድራሻዎ ያለበት ዶኩሜንት

### የተፈቀዱ የስዕል ወይም የፎቶ የመታወቅያ ወረቀቶች

*ከሚከተሉት ኣንዱን ይምረጡ፡ ግዜው ያለፈበትም ሊሆን ይችላል።*

የመንጃ ፍቃድ፡ የክፍለሃገሩ የመታወቅያ ወረቀት ወይም በማናቸውም ክፍላተ ሃገር የተሰጠ የለማጅ ፍቃድ

የኣሜሪካን ፓስፖርት

የኣሜሪካን የውትድርና ወይም የኣሜሪካ የቀድሞ ወታደሮች መታወቅያ ወረቀት

ስም፡ ፊርማና ፎቶ/ስዕል ያለበት የጎሳ መታወቅያ ወረቀት

የሚኖሶታ ዩኒቨርሲቲ፡ ኮሌጅ  ወይም የተግባረ እድ ትምህርት ቤት መታወቅያ ወረቀት

የሚኖሶታ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመታወቅያ ወረቀት

### የተፈቀዱ ዶኩሜንቶች

*ኣንዱን ይምረጡ፡ የመረጡትን በኤሌክትሮኒክ መሳርያም ማሳየት ይቻላል።*

ምርጫው ቀን በፊት ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የተገኙ ደረሰኞች፡ከታች ከተዘረዘሩት ኣገልግሎት ሰጪዎች፡ ኣገልግሎት ማግኘት የጀመሩበት የክፍያ ወረቀቶች፡

- * የቴሌፎን፡ የቴሌቪዥን ወይም የኢንተርኔት
- * የቁሻሻ መጣያ፡ የጽዳት ኣገልግሎት፡ የመብራት፡ የጋዝ ወይም የውሃ ደረሰኞች
- * የባንክ ሂሳብና የብድር ወረቀት
- * የቤት ኪራይ ወይም የቤት መግዣያ ዕዳ

እስከ ምርጫው ቀን ድረስ የሚዘልቁ የቤት ኪራይ ስምምነቶች

ወቅታዊ የሆኑ የተማሪዎች የትምህርት ክፍያዎችን የሚያመለክቱ ጽሁፎች

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE

# የምርጫ ቀን ምዝገባ

VOTE 2025

...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ

## ③ የመኖርያ ቤትዎን ትክክለኛ ኣድራሻ የሚመሰክር የተመዘገበ መራጭ

በኣካባቢዎ የሚኖር የተመዘገበ መራጭ ወደ ምርጫው ቦታ ኣብሮ ከእርስዎ ጋር በመሄድ፡ ያሉበት ኣድራሻ ትክክለኛው ኣድራሻዎ መሆኑን በመሃላ በመፈረም ሊመሰክርልዎ ይችላል። ይህም "ቫውቺንግ" በመባል ይታወቃል። ማንኛውም ለመምረጥ የተመዘገበ ሰው፡ ቁጥራቸው እስከ ስምንት ለሚደርስ ሰዎች ሊመሰክር ይችላል። ሌላ ሰው ለእርስዎ ከመሰከረልዎ ግን እርስዎ ለሌላ ሊመሰክሩ ኣይችሉም።

## ④ በኮሌጅ ውስጥ የሚኖሩ የኮሌጅ ተማሪዎች የመኖርያ ቤት ዝርዝር

የኮሌጆችና የዩኒቨርሲቲዎች ባለስልጣናት፡ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎችን ዝርዝር ለኣስመራጭ ኮሚቴዎች ይልካሉ። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ስምዎ ካለ፡ የኮሌጁ የመታወቅያ ወረቀት በማሳየት ምዝገባውን ማጠናቀቅ ይችላሉ።

## ⑤ ህጋዊ የሆነ ምዝገባ በኣካባቢው

በኣንድ ኣካባቢ ከተመዘገቡ በውሃላ፡ ስምዎን ወይም የሚኖሩበትን ኣድራሻ በዛው ኣካባቢ ውስጥ ከቀየሩ፡ ለኣስመራጭ ዳኛው፡ የቀድሞ ስሞን ወይም የቀድሞ ኣድራሻዎን ብቻ ነው መንገር ያለብዎ።

## ⑥ ዘግይቶ ስለመመዝገብ የተሰጠ ማስታወቅያ

ዋናው ምርጫ ከመካሄዱ በፊት ባሉት 20 ቀናት ውስጥ ለመምረጥ ከተመዘገቡ፡ ዘግይቶ የተመዘገበ የሚል ማስታወቅያ ወረቀት ይላክሎት ይሆናልና ይህንን ወረቀት ከእርስዎ ጋር ወደ ምርጫ ጣብያው ይዘው በመሄድ፡ የሚኖሩበትን ቦታ ለማሳየት ወረቀቱን እንደ ኣንድ ማረጋገጫ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

## ⑦ የጋራ መኖርያ ቤቶች የኣስተዳደር ክፍል ሰራተኛ

በጋራ መኖርያ ቤቶች የሚቀመጡ ከሆነ የመኖርያ ቤቶቹ የኣስተዳደር ክፍል ሰራተኛ ከእርስዎ ጋር ወደ ምርጫው ጣብያ በመሄድ የሚኖሩበትን ኣድራሻ ሊያረጋግጥልዎ ይችላል። ይህም "ቫውቺንግ" በመባል ይታወቃል። የእነዚህ ዓይነቶቹ መኖርያዎች የኣስተዳደር ክፍል ኣባል፡ ለእያንዳንዱ ነዋሪ ምስክርነት ሊሰጥ ይችላል።

*የሚኖሶታ የኣገር ውስጥ ኣስተዳደር ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት*

mnvotes.gov • 1-877-600-VOTE